ትኩረት/EXHIBIT

ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

# የስነ ምግባር እና የዜግነት አላማዎች

**የስነምግባር/ባህርይ አላማዎች**

1. ለእውነት አክብሮት በመስጠት የእውቀት ጉጉት እና የትምህርት ፍቅር ላይ የተመሰረተ የግል ታማኝነት እና ሐቀኝነት

2. ለራስ፣ ለቤተሰብ፣ ለት/ቤት እና ለማህበረሰብ የሃላፊነት ስሜት

3. የራስን አቅም በመረዳት ላይ የተመሰረተ ከፍተኛ አድናቆት

4. ዘር፣ ሀይማኖት፣ ጾታ፣ ዕድሜ፣ አካላዊ ወይም የአዕምሮ ሁኔታ ሳይገድብ የሁሉንም ሰዎች መብት ማክበር

5. በተፎካካሪ አስተያየቶች መካከል አድሎአዊ ፍርድ የመስጠት አቅም ጋር ተዳምሮ የሌሎችን የተለያዩ አመለካከቶችን የመያዝ እና የመግለጽ መብቶችን እውቅና መስጠት

6. የፍትሃዊነት ስሜት፣ትክክለኛነት፣ በሐቅ እና በደንቡ መሠረት መሥራት እና እነርሱን ለማክበር ያለ የቁርጠኝነት ስሜት

7. ሌሎችን የመረዳት፣ የመተሳሰብ፣ እና የመረዳዳት/የመተጋገዝ ዝንባሌ

8. ዲሲፕሊን የተሞላበት ስሜት እና ሌላ ሰው የሰራውን በኩራት መግለጽ፣ የሌሎችን ስኬቶች ማክበር

9. የህዝብ ንብረትን ጨምሮ የለሌሎችን ንብረት ማክበር/መንከባከብ

10. የራስን ፅኑ እምነት የመግለጽ ድፍረትና ብቃት

**የዜግነት ዓላማዎች**

1. ለዩናይትድ ስቴትስ ኦቭ አሜሪካ የአገር ፍቅር ስሜት፣ ፍቅር፣ አክብሮት እና ታማኝነት እና ጉድለቶችን በሕጋዊ መንገድ ለማስተካከል ፈቃደኛ መሆን

2. በዲሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ውስጥ የአንድን ዜጋ መብቶች እና ግዴታዎች ግንዛቤ መጨበጥ
3. በዓለም ላይ ያሉ በዲሞክራሲያዊ መንግስት የማይተዳደሩ ማህበረሰቦች ያላገኙትን መብቶች ግንዛቤ መውሰድ

4. የ ዩ. ኤስን ህገ መንግስት ማክበር፣ የህግ የበላይነት እና እያንዳንዱ ዜጋ በህግ ፊት እኩል መብት እንዳለው/እንዳላት ማወቅ። ስለ መብቶች ህግን መረዳት እና ሁሉም መብቶች በሌሎች መብቶች እና ግዴታዎች የተገደቡ መሆናቸውን ማወቅ

5. በአካባቢ፣ በስቴት እና በፌደራል ደረጃ ህጋዊ ስልጣንን ማክበር

6. ከአንድ ፓርቲ አምባገነናዊ አገዛዝ በተቃራኒ ለዲሞክራሲያዊ መንግስት ጽንሰ ሃሳብ ታማኝ መሆን። ዲሞክራሲያዊ መንግስት የሚገደበው በስልጣን ክፍፍል እና በሌሎች ተቋማት የሥልጣን መጋራትና ማካካስ በብዙሃን ማህበረሰብ ውስጥ ያላቸውን ሚና ሚዛናዊነት በማስጠበቅ ሲሆን - በዋናነት ቤተሰብ፣ ሃይማኖት፣ ትምህርት ቤት እና የግሉ ዘርፍ ኢኮኖሚ ናቸው።

7. የዜጎችን መብት ለመጠበቅ ነጻ ለሆነ የፍትሕ ስርዓት አስፈላጊነት እውቅና መስጠት

8. በአካባቢ፣ በስቴት እና በብሔራዊ ደረጃ ያሉትን ሁሉንም የዜግነት ኃላፊነቶች መቀበል እና ዩናይትድ ስቴትስን እና የዴሞክራሲ ተቋሞቿን ለመጠበቅ እና ለመከላከል ቁርጠኝነት ማሳየት